# ቀደም ሲል በተሰጡት የጥፋተኝነት ውሳኔዎች ምክንያት ስለሚከብዱ ወንጀሎች ክስ አቀራረብ የተለየ ሥነ ሥርዓትና ዓላማው ፤ በማናቸውም ሁኔታ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ወይ ?

በዮሴፍ ገብረ እግዚአብሔር*

የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ ፩፻፲፬ ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች ምክንያት ከባድ ቅጣት ስለሚያስቀጡ ወንጀሎች የተለየ የክስ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት ይደነግጋል ። በዚህ አንቀጽ መሠረት አንድ ተከሳሽ ፈጸመ የተባለው ወንጀል ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች ምክንያት ከባድ ቅጣት ያስቀጣዋል ከተባለ ቅጣትን በሚያከብደው ወንጀል አይከሰስም ። መከሰስ ያለበት ቅጣቱን በማያከብድበት ወንጀል ነው ። አቃቤ ሕጉ ተከሳሹ ቀደም ሲል የጥፋተኛነት ውሳኔ ተሰጥቶበት የነበረ መሆኑን ማስረዳት ያለበት ተከሳሹ በተከሰሰበት ቅጣትን በማያከብደው ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ብቻ ነው ።

በዚህ አንቀጽ ላይ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ ተከሳሹን ቅጣቱን በሚያከብደው ወንጀል መከሰስ ሲቻል ለምን የተለየ ሥነ ሥርዓት አስፈለገ ? የሚለው ነው ። ለዚህ ጥያቄ ግልጽ ሆኖ የሚታየው መልስ ፤ ክስ በፍርድ ቤት እንዲሰማ የሚደረግበት ምክንያት ወንጀል ተፈጽሞ እንደሆን ለማስረዳት ነው ። ይኸውም ፤ አንድ ተከሳሽ ቀደም ሲል በፈጸመው ወንጀል ጥፋተኛነቱ በፊት የተወሰነ ስለሆነ እንደገና ማስረዳት አስፈላጊ አይሆንም ። በክስ ማመልከቻ መገለጽና በማስረጃ መረጋገጥ ያለበት አዲሱ የወንጀል ክስ ብቻ ነው ። ቀደም ሲል የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበት ነገር በአዲሱ የክስ ማመልከቻ ላይ መገለጽ የለበትም የተባለው ስለዚህ ነው የሚል ሊሆን ይችላል ።

ሆኖም ይህን የተለየ ሥነ ሥርዓት መቀየስ ያስፈለገው ከላይ በተገለጸው ምክንያት ብቻ ነው ለማለት አስቸጋሪ ይሆናል ። ዓቃቤ ሕጉ ተከሳሹ "... ከዚህ ቀደም በወንጀል የተቀጣበትን ለፍርድ ቤት ማስረዳት ..."[1] እንዳለበት ተደንግጓል ። ይህ ሲታይ ልዩ ሥነ ሥርዓት ያስፈለገበት ምክንያት ከላይ የተገለጸው ብቻ ቢሆን ኖሮ ቀደም ሲል የጥፋተኛነት ውሳኔ የተሰጠበትን ወንጀል ዓቃቤ ሕጉ ክሱ በፍርድ ቤት በሚሰማበት ጊዜ ከጥፋተኛነት ውሳኔ በኋላ ብቻ ማስረዳት እንዳለበት መደንገጉ ባላስፈለገም ነበር ። ስለዚህ ዓቃቤ ሕጉ ቀደም ሲል የተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎችን ማስረዳት ያለበት ተከሳሹ በተከሰሰበት ቅጣትን በማያከብደው ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ በኋላ ነው ተብሎ የተደነገገበት ሌላ ምክንያት መኖር አለበት ።

የተለየ ሥነ ሥርዓት ያስፈለገበት ምክንያት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁ. ፩፻፴፰ የተደነገገውን መሠረታ ሐሳብ ተግባራዊ ለማድረግ መስሎ ይታያል ። በዚህ አንቀጽ መሠረት ፤ በሕግ በተለየ ሁኔታ ካል ተደነገገ በስተቀር[2] ተከሳሹ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ መሆኑ ካልተረጋገጠ ፤ ቀደም ሲል ውሳኔ የተሰጠባቸው ጥፋቶች ለፍርድ ቤቱ መገለጽ የለባቸውም ፤ በቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍርድ ቤት መዝገብ ውስጥም መገለጽ የለባቸውም ።

የቁ. ፩፻፴፰ ዓላማ ክሱን የሚሰማው ፍርድ ቤት በተከሳሹ ላይ አስቀድሞ የጥፋተኛነት ግምት እንዳያሳድር ለመከላከል ሆኖ ይታያል ። ፍርድ ቤቱ ክሱን ከመስማቱ በፊት ተከሳሹ ከክሱ በፊት የፈጸማቸው ወንጀሎች መኖራቸውን ካወቀ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ፈጽሟል ወይስ አልፈጸመም?[3] የሚለውን ጭብጥ በመያዝ በንጹሕ ሕሊና ማስረጃውን መመርመር ሲገባው ተከሳሹ ይህንንም ወንጀል ሳይፈጽም አይቀርም

* ሌክቸረር ፤ ሕግ ፋኩልቲ ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

1 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ 114(2)

2 "ሕጉ በተለይ በግልጽ ካልፈቀደ በቀር" የሚለው ሐረግ የማስረጃ ሕግን ለማስመልከት የታቀደ ይመስላል ። በዚህ ቁጥር የተደነገገው ሕግ "ኮመን ሎውን" በሚከተሉ ሐገሮች የማስረጃ ሕግ ነው ። ይህን ለመገንዘብ ፒ ኤን ራማስዋሚ እና ኤስ ራጀግፓላን ፤ ውድርፍ ኤንድ አሚር ኦሲስ ሎው ኦፍ ኤቪደንስ ኢን ኢንድያ (ሎው ቡክ ካምፓኒ አላሃባድ ፤ ፲፩ኛ እትም እ ኤ አ ፲፱፻፷፪) ቮልዩም 2 ገጽ 11597 እና ጂ.ዲ.ናክስ ፤ አን ኢንትሮዳክሽን ቱ ኤቪደንስ (ለንደን ስዊት ኤንድ ማክስዌል ፪ኛ እትም እ ኤ አ ፲፱፻፷፫) ገጽ 136-41 ይመለከቷል ። የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓታችን የውጭ ሀገር ሕግ ምንጮች ኮሞን ሎው እና ሲቪል ሎው ለመሆናቸው ፤ ስታሊን ዜድ ፊሸር ፤ ኢትዮፕያን ክሪሚናል ፕሮሲጀር ኤ ሶርስ ቡክ (ሕግ ፋኩልቲ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከእክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ጋር በመተባበር ያሳተመው ፤ እ ኤ አ ፲፱፻፷ ዓ/ም) ገጽ 4-12 (ታሪካዊ መግቢያ) ይመለከቷል ። ስለሆነም የሲቪል ሎውን ይዘት በመከተል በሥነ ሥርዓት ሕግ የማስረጃ ሕግ ተደንግጎ እናያለን ። ይህ የሲቪል ሎው አሠራር ስለመሆኑ ስለ ማስረጃ የሚደነግጉት ነገር ግን በፍትሐ ብሔር ሕግ የሚገኙት የፍትሐ ብሔር ሕጎችን ቁ 2001-2021 ይመለከቷል ።

3 የበፊት ጥፋቶች ከጥፋተኛነት ውሳኔ በፊት የማይገለጹበት ምክንያት ይህ ለመሆኑ ጆን ኤች.ዊግሞር ፤ ኤ ትሪቲስ ኦን ዘ አንግሎ አሜሪካን ሲስተም ኦፍ ኤቪደንስ ኢን ትራያልስ አት ኮሞን ሎው (ቦስቶን ፤ ሊትል ፤ ብራውን ኤንድ ኮምፓኒ ፤ ፫ኛ እትም ፤ እ ኤ አ ፲፱፻፵) ቮልዩም ፩ ገጽ 412-415 እና 454-456 ይመለከቷል ።

ወደሚል ግምት እንዳያመራ ለመከላከል የታቀደ ሆኖ ይታያል ። የፖሊስ ምርመራ መዝገብ በቁ ፩፻፴፰ አለመጠቀሱም ሲታይ ይህ አንቀጽ እንዲከላከል የታቀደው ይህን ክሱን የሚሰማ ፍርድ ቤት ሊያድርበት የሚችለውን ከላይ የተገለጸውን ግምት መሆኑን ያመለክታል ። የቀዳሚ ምርመራ መዝገብ ክሱን ለመስማት ብቸኛ ሥልጣን ላለው ለከፍተኛው ፍርድ ቤት[4] በፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር በኩል መቅረብ አለበት ። የወንጀል ክሶችን በሚመለከት አንፃር ፣ የሬጅስተሩ ሥልጣን ለችሎቶች ማከፋፈል እንደመሆኑ ፣ የቀዳሚ ምርመራ መዝገብ ክሱን ለመስማት ሥልጣን ወዳለው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ችሎት[5] በሬጅስትራሩ አማካይነት መተላለፍ እንዳለበት የታወቀ ነው ። የፖሊስ ምርመራ ራፖር ግን መላክ ያለበት ለዐቃቤ ሕጉ[6] ነው ። በመሠረቱ ፣[7] የፖሊስ ምርመራ ራፖርን በሚመለከት ረገድ ክሱ በሚሰማበት ጊዜ በነገሩ አግባብ ካላቸው መካከል ዐቃቤ ሕጉ ብቸኛ ሥልጣን አለው ። ከተጠቀሰው አንቀጽ በግልጽ እንደሚታየውም ፣ ዐቃቤ ሕጉ የጥፋተኛነት ውሳኔ ለማስገኘት መተማመን ያለበት ቀደም ሲል በተከሳሹ በተሰጡ የጥፋተኛ ውሳኔዎች ሳይሆን ተከሳሹ ፈጽሟል ተብሎ በተከሰሰበት ወንጀል ተመርምሮ በተገኘው ማስረጃ ብቻ ነው ። ስለዚህ ፣ ቀደም ሲል የተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች መኖራቸው በቀዳሚ ምርመራ መዝገብ ከተገለጸ ክሱን የሚሰማው ፍርድ ቤት ክሱን መስማት ከመጀመሩ በፊት ተከሳሹ ቀደም ሲል ወንጀል መፈጸሙን ያውቃል ፤ ካወቀም ይህንንም ወንጀል ሳይፈጽመው አልቀረም የሚል ግምት ሊያሳድርበት ይችላል ። ከሆነም የቁ. ፩፻፴፰ ዓላማን የሚቃረን ይሆናል ።

የፖሊስ ምርመራ ራፖርን በሚመለከት ረገድ ግን በራፖሩ ሥልጣን ያለው ዐቃቤ ሕግ በመሆኑ ቀደም ሲል የተሰጡ የጥፋተኛ ውሳኔዎች በፖሊስ ምርመራ ራፖር ቢገለጹ ክሱ በትክክለኛ መንገድ እንዳይታይ ሊያደርገው አይችልም የሚል እምነት ያለ ይመስላል ።[8] ቅጣትን ለማክበድ ቀደም ሲል የተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች ካሉ መጠቀስ ያለባቸው ተከሳሹ ጥፋተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ቅጣት ከመወሰኑ በፊት ነው ። ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች ምክንያት ስለሚከብዱ ወንጀሎች ክስ አቀራረብ የተለየ ሥነ ሥርዓት መደንገግ ያስፈለገበት ምክንያት በቁ. ፩፻፴፰ የተደነገገው ዓላማ ተግባራዊ ሆኖ ክሱ በገለልተኛነት እንዲሰማ ለማድረግ ባይሆን ኖሮ የተለየ ሥነ ሥርዓት ባለስፈለገም ነበር ።

አንድ ተከሳሽ ልማደኛ ወንጀለኛ መሆን አለመሆኑን ማስረዳት የሚቻለው ቀደም ሲል የተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎችን በማስረዳት መሆኑ ግልጽ ነው ። በአንድ በንብረት ላይ በሚፈጸም ወንጀል የተጠረጠረ ግለሰብ ሲያዝና ምርመራ ሲደረግ ድርጊቶቹ የተለያዩ ወንጀሎች ናቸው ሊያሰኝ በሚያስችል "አዲስ ጥፋት"[9] ተደጋጋሚ የስርቆት ወንጀሎች ፈጽሞ ሊገኝ ይችላል ። እንደዚሁ በሚሆንበት ጊዜ ቅጣት የሚወሰነው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥሮች ፹፩ እና ፩፻፹፱ በመሆኑ ምንም እንኳን ውጤቱ ቅጣትን ማክበድ ቢሆንም ቅጣቱ የሚከብደው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ. ፩፻፹፱ እንጂ ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች ምክንያት አይደለም ። ቀደም ሲል የተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች አንድ ወንጀለኛ የወንጀሉን ድርጊት እንደሞያ ሥራው አድርጎ የሚጠቀምበት መሆን አለመሆኑን ለመወሰንም ይረዳሉ ። ለምሳሌ ያህል አንድ በማስወረድ ወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ወንጀለኛ በዚህ ወንጀል የበፊት ጥፋቶች ያሉት መሆኑን ዐቃቤ ሕጉ ለማስረዳት ከቻለ ክሱን የሚመረምረው ፍርድ ቤት ወንጀለኛው የማስወረድ ወንጀልን እንደ ሞያው አድርጎ የሚጠቀምበት መሆኑን ለመወሰን ይችላል ።

ከላይ እንደተገለጸው ሁሉ ዐቃቤ ሕጉ አንድ ተከሳሽ ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች ምክንያት በከባድ ወንጀል የጥፋተኛነት ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል የሚል እምነት ካደረበት ፣ ተከሳሹ መከሰስ ያለበት ቅጣት በማያከብደው ወንጀል ሆኖ ክሱ መቅረብ ያለበት ቅጣቱን የሚያከብደውን ወንጀል ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ነው ። ስለዚህ በቁ. ፩፻፴፰ የተገለጸው ዓላማ ግቡን እንዲመታ ለማድረግ የታቀደው ልዩ ሥነ ሥርዓት ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚችለው ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች ምክንያት የሚከብዱ ወንጀሎችን ክስ የሚያየው ፍርድ ቤት እና ቅጣትን የማያከብዱት ወንጀሎችን ክስ የሚያየው ፍርድ ቤት አንድ ሲሆን ነው ።

የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች ምክንያት የሚከብዱ ወንጀሎችን በሁለተኛው ታላቅ ክፍል በሚገኙት በተለያዩ ቁጥሮች ይደነግጋል ።

በዚህ በሁለተኛው ታላቅ ክፍል የሚገኙት ቁጥሮች ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች ምክንያት የሚከብዱ ወንጀሎችን የሚገልጹ ሐረጎች "የዘ

4 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ 80(2)

5 ዐቃቤ ሕጉ ጥፋተኛ ለማድረግ በቂ ማስረጃ የሌለ መሆኑን የተገነዘበ እንደሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ 42(1) (ሀ) መሠረት ክስ አላቀርብም የማለት ግዴታ አለበት ። ምንም እንኳን ይህ ቁጥር የቀዳሚ ምርመራ መዝገብን ባይጠቅስም ፣ የሥነ ሥርዓቱ ሕግ ቁ ፹/፪ እና ፩፻፱(፩) ብንመረምር ቁ ፺፪(፩) (ሀ) በቂ ማስረጃ በማያመለክት ቀዳሚ ምርመራ መዝገብም ተፈጻሚ መሆን ይኖርበታል ። በዚህ ነጥብ ፣ ፒ ግራቨን "ላኖቬል ፕሮሲጀር ፔናል ኢትዮፒየን ፣" ሪብ ፔናል ስዊስ ፸፱ኤ እ ኤ አ ፲፱፻፷፫ የግርጌ ማስታወሻ ቁ ፳፱ በስታንሌ ዜድ ፊሸር ፣ ኢትዮፒያን ክሪሚናል ፕሮሲጀር ኤ ሶርስ ቡክ (ሕግ ፋኩልቲ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከእክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ጋር በመተባበር ያሳተመው እ ኤ አ ፲፱፻፷፱ ዓ/ም) ፣ ገጽ 200 ይመለከቷል ።

6 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ ፴፯(፪)

7 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ ፩፻፵፩ትን ይመለከቷል ።

8 ትክክለኛ የሆነ ምርመራን በሚመለከት አንፃር የበፊት ጥፋቶች አጉል ግምት ሊያሳድሩ አይችሉም ወይ ? የሚል ጥያቄ ለመጠየቅ ይቻላል ። ሆኖም ሕጉ በዚህ ነጥብ የደነገገው የለም ።

9 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ 60-63 ይመለከቷል

ወትር የሞያ ሥራው ያደረገ" (በመንግሥቱ የቀረጥና የግብር ገቢዎችና በጠቅላላ የገንዘብ ጥቅሞቹ ላይ ስለ ሚሠሩ ወንጀሎች ቁ. ፫፻፷፩) ፣ "ልማዳዊ ወይም የሞያ ሥራ ሆኖ የተያዘ ጉዳይ" (ግልጽ በሆኑ ገንዘቦች ፣ ማሕ ተሞች ቴምብሮችና መሣሪያዎች ላይ ስለሚሠሩ ወን ጀሎች ቁ. ፫፻፹፩ (፩)) ፣ "ሞያው አድርጎ ይዞት እንደ ሆነ" (በሕዝብ ጥቅሞችና በማሕበራዊ ኑሮ ላይ ስለሚ ሠሩ ወንጀሎች ፣ የንግድ ዕቃዎችን ወደ ሐሰተኛነት ስለ መለወጥ ፣ ቁ. ፬፻፪ (፩)) ፣ "እንደ ሞያ ሥራው አድርጎ የያዘ እንደሆነ" (በቁ. ፭፻፲፩ እና ፭፻፲፮ ለተገለጹት ወን ጀሎች ማክበጃ) ) ፣ "የማስወረድን ተግባር ሥራው አድርጎት እንደሆነ" (የማስወረድ ወንጀል ማክበጃ) ፣ "ሞያ አድርጎ የያዘ" (በመልካም ጠባይና በቤተ ዘመድ ላይ ስለሚደረጉ ወንጀሎች ፣ ቁ. ፮፻፩ (፩) (ለ)) ፣ "ሞያ ተብሎ በተያዘው አቃጣሪነት" (በመልካም ጠባይና በቤተ ዘመድ ላይ ስለሚደረጉ ወንጀሎች ፣ በሌላ ሰው አመንዝራነት ስለ መጠቀም ቁ. ፮፻፯) ፣ "ስርቆት ፣ ወይም ሌሎች ወንጀሎችን ሥራው አድርጎ የያዘ እንደሆነ" (በሀብት ላይ ስለሚሠሩ ወንጀሎች ፣ ቁ. ፮፻፴፮ (፫))(ሀ)) " የጦር መሣሪያ ይዞ የወንበዴነት ወንጀል መሥራትና ወንበዴዎችም ባንድ ክፍል የተቋቋሙ የውንብድና ማህበረተኞች የሆኑ እንደሆነ" (በሀብት ላይ ስለሚሠሩ ወንጀሎች ፣ ቁ. ፮፻፴፯ (፪) ሁለተኛው አዲስ መስመር) ፣ "ያታላይነት ሥራ ሞያው አድርጎት እንደሆነ" (በንብ ረት መብቶች ላይ ስለሚሠሩ ወንጀሎች ፣ ቁ. ፮፻፶፰ (ሁ)) እና "እንደ ሞያ ሥራው አድርጎ ይዞአል በሚያሰኝ ሁኔታ" (በንብረት መብቶች ላይ ስለሚሠሩ ወንጀሎች ቁ ፮፻፸ (ሀ)) ናቸው ።

እነዚህን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የሁለተኛውን ታላቅ ክፍል ቁጥሮችን ስንመረምር ፣ ቀደም ሲል በተሰጡ የጥ ፋተኛነት ውሳኔዎች ምክንያት ወንጀል ለማክበድ ሁለት መንገዶች መቀየሳቸውን እንገነዘባለን እነዚህም ፦

ሀ/ ወንጀል የማክበድ ሁኔታን የሚያስከትሉ ድርጊ ቶች በአንድ የልዩ ክፍል ቁጥር ዘርዝሮ በመግለጽ እነዚህ ድርጊቶች ሲሟሉ ከአንድ ፍርድ ቤት ሥልጣን ውጭ ሊሆን በማይችለው ቅጣቱን በማያከብደው ወን ጀል ተከሶ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው ወንጀለኛ ቅጣቱ እንዲከብድበት በመደንገግ ፤[10]

ለ/ ወንጀል የማክበድ ሁኔታን የሚያስከትሉ ድርጊ ቶች በአንድ የልዩ ክፍል ቁጥር ዘርዝሮ ይህን የልዩ ክፍል ቁጥር ራሱን የቻለ ከባድ ወንጀል በማድረግ ቅጣ ቱን ከማያከብደው ወንጀል በመለየት ። በዚህ መንገድ የተለዩት ቅጣትን የማያከብዱ ወንጀሎች ክስ እና ቅጣ ትን የሚያከብዱ ወንጀሎች ክስ የማየቱ ሥልጣን በአ ንድ ፍርድ ቤት ወይም በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ሊሆን ይችላል ።[11]

ቅጣቱን የሚያከብዱ ሁኔታዎች የተደነገጉት ከላይ በፊደል (ሀ) በተገለጸው መንገድ ሲሆን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ ፩፻፴፰ ዓላማ ምንጊዜም ቢሆን ተግባራዊ ይሆናል ። ይህ የሚሆንበት ምክንያ ትም የልዩ ክፍሉ ቁጥር የተደነገገው የተለየ ወንጀልን ለመወሰን ሳይሆን በክፍሉ የተመለከቱት ወንጀሎች ቅጣትን በሚያከብድ ሁኔታ ሲፈጸሙ ቅጣቱ እንዴት መክበድ እንዳለበት በአጠቃላይ ክፍሉን የሚመለከቱ የማክበጃ ሁኔታዎች የሚደነገግ ስለሆነ እንደዚህ ዓይ ነቱ አንቀጽ የፍርድ ቤቶችን ሥልጣን በሚመለከት ረገድ የተወሰነ አንድ ፍርድ ቤት ብቻ እንዲያየው ሊደ ረግ የማይቻል በመሆኑ ነው ። ስለዚህ ቀደም ሲል በተ ሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች ምክንያት ቅጣቱ የሚያ ከብድ ክስ ወይም ቅጣት የማያከብድ ክስ ያው ሥልጣኑ የተወሰነው በአንድ ፍርድ ቤት ብቻ ስለሆነ ፣ አንድ ተከሳሽ ቅጣትን በማያከብድ ወንጀል ተከሶ በመቅረቡ ብቻ ፍርድ ቤቱ ይህ የሆነው ቀደም ሲል በተሰጡ የጥ ፋተኛነት ውሳኔዎች ምክንያት መሆን አለበት የሚል ግምት ለመውሰድ አይችልም ፡፡

ቅጣትን የሚያከብዱ ሁኔታዎች የተደነገጉት ከላይ በፊደል (ለ) በተገለጸው መንገድ ሲሆን ግን ቅጣት የማ ያከብደውን ወንጀል እና ከባዱን ወንጀል ለማየት ሥል ጣን ያለው ፍርድ ቤት አንድ ፍርድ ቤት ካልሆነ የወ ንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ. ፩፻፴፰ ዓላማ በተለየው ሥነ ሥርዓት ምክንያት ተግባራዊ ሊሆን አይ ችልም ። ይህንንም የተለየው ሥነ ሥርዓት ከሚደነግ ገው ከቁ ፩፻፲፬ ራሱ ለመገንዘብ ይቻላል ። ቅጣት የማያ ከብደውን ወንጀል እና ከባዱን ወንጀል ለማየት ሥል ጣን ሊኖራቸው የሚችል ፍርድ ቤቶች በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ ይኸው አን ቀጽ ጠቋሞ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ቀደም ሲል በተሰ ሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች ምክንያት ቅጣትን በሚ ያከብድ ወንጀል መቀጣት ያለበት ተከሳሽ መከሰስ ያለ በት ቅጣትን በማያከብደው አንቀጽ ሆኖ ክሱ ግን መቅ ረብ ያለበት ቅጣትን የሚያከብደውን ወንጀል ለማየት ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት መሆን እንዳለበት ይደነ ግጋል ።

ይህንንም ሁኔታ በይበልጥ ለማብራራት ፣ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ. ፮፻፴፯ (፭) የተደነገገውን እንመልከት ። ለጊዜው የዚህን ቁጥር ንኡስ ቁጥር ፩ (ለ)ን ወደ ጎን በመተው ሌሎቹን የቅጣት ማክበጃ ሁኔታዎች ብንመ ረምር ፣ በክስ ማመልከቻው መዘርዘር ያለባቸውና ክሱ በሚሰማበት ጊዜም በማስረጃ መረጋገጥ ያለባቸው ሆነው እናገኛቸዋለን ። ይህም የሚሆንበት ምክንያት የወንጀሉ መክበድ የተመሠረተው ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተ ኛነት ውሳኔዎች ባለመሆኑ ነው ። በዚሁ ቁጥር ንኡስ ቁጥር ፩ (ለ) የተደነገገውን ስንመለከተው ግን የቅጣቱ ማክበጃ ምክንያት ቀደም ሲል የተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች መሆናቸው በግልጽ ይታያል የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ. ፮፻፴፯ ሥልጣን የአውራጃ ፍርድ ቤት የቁ. ፮፻፴፯ ደግሞ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢሆን ኖሮ ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች ምክንያት በቁ. ፮፻፴፯ መቀጣት የሚገባው ተከሳሽ መከሰስ ያለበት

10 ለምሳሌ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፫፻፷፩ እና ፫፻፹፩ን ይመለከቷል ።

11 ለምሳሌ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ ፮፻፰ እና ፮፻፴፩ እና ፮፻፴፯ እና ፮፻፴፰ን ይመለከቷል ።

በቁ. ፯፻፴፯ ሆኖ ክሱ ግን መቅረብ ይኖርበት የነበረው በከፍተኛ ፍርድ ቤት ይሆን ነበር ። ነገር ግን ፣ ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች ምክንያት በቁ. ፯፻፴፯ ለመቀጣት አንድ ተከሳሽ በቁ. ፯፻፴፯ መከሰስ ይኖርበታል ። በመሆኑም ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተከሳሹ በቁ. ፯፻፴፯ ተከሶ የቀረበው ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች ምክንያት ብቻ መሆኑን በግልጽ ሊያውቅ ይችላል ማለት ነው ።

ቅጣት የማያከብደውን እና የሚያከብደውን የወንጀል ክስ ለማየት ሥልጣን የተሰጠው አንድ ፍርድ ቤት ብቻ ቢሆን ኖሮ ይህ የቁጥር ፩፻፴፰ ዓላማ ተግባራዊ አለመሆን በቲኦሪ ደረጃ ብቻ የሚያከራክር ሆኖ ይቀር ነበር ። ይህ መሆን አለመሆኑን ለመረዳት እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ወንጀሎች በሚመለከት ረገድ የፍርድ ቤቶች የሥልጣን ክፍፍል መመርመር አስፈላጊ ነው ።

የተሰረዘው ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት አንደኛ ሰንጠረዥን ስንመለከት ከላይ በፊደል (ለ) በተ ገለጸው መንገድ ከተመደቡት ወንጀሎች ውስጥ ከከባድ ለተፈጥሮ ግብር ተቃራኒ የሆነ የአመንዝራነት ሥራ (ቁ. ፯፻፮ (፩) (ለ)) እና ከከባድ ስርቆት (ቁ. ፮፻፴፮ (፫) (ሀ)) በስተቀር ቅጣትን የማያከብዱትን እና የሚ ያከብዱትን ወንጀሎች ለማየት ሥልጣን የተሰጠው ፍርድ ቤት አንድ ሆኖ እናገኘዋለን ። ስለዚህ እነዚ ህን ወንጀሎች በሚመለከት ረገድ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ. ፩፻፴፰ ዓላማ ምንጊዜም ቢሆን ተግባራዊ ይሆናል

ከዚህ ከተሰረዘው አንደኛ ሰንጠረዥ እንደሚታየው ፣ ከባድ ለተፈጥሮ ግብር ተቃራኒ የሆነ አመንዝራነትን እና ከባድ ስርቆትን በሚመለከት ረገድ የቀድሞ የፍ ርድ ቤቶች ክስን የማየት ሥልጣን ክፍፍል የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ. ፩፻፴፰ትን ዓላማ ያፈርሰዋል ።

የተሻሻለው የፍርድ ቤቶች ሥልጣን ክፍፍል ግን[12] የተፈጥሮ ግብር ተቃራኒ የሆነ አመንዝራነትንና ማከ በጃውን ወንጀል የማየት ሥልጣን የአውራጃ ፍርድ ቤት ብቻ እንዲሆን በመወሰን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ ፩፻፴፰ ዓላማ ተግባራዊ እንዲሆን አድርጎ ታል ። ይሁን እንጂ ሥርቆትን እና ከባድ ስርቆትን በሚመለከት ረገድ ማሻሻያው ሕግ ስርቆት የወረዳ ፍርድ ቤት ሥልጣን ፣ ከባድ ስርቆት ደግሞ የአውራጃ ፍርድ ቤት ሥልጣን እንዲሆን በመወሰኑ ፣ አውራጃው ፍርድ ቤትም ፣ ምንም እንኳን ክሱን መስማት ከመ ጀመሩ በፊት ተከሳሹ አሁንም እንደአመሉ የተከሰሰ በትን ድርጊት ሳይፈጽም አይቀርም የሚል ግምት ሊያ ድርበት የሚችል ቢሆንም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ ፩፻፲ መሠረት የስርቆትን ክስ የመቀበል ግዴታ ስላለ በት የስርቆት ወንጀልን በሚመለከት ረገድ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ ፩፻፴፰ ዓላማ ምን ጊዜም ተግባራዊ ሊሆን አይችልም ። ታዲያ ይህ ግምት በተ ከሳሹ ላይ ለሚሰጠው የጥፋተኛነት ውሳኔ ምክንያት ሊሆን አይችልም ማለት ይቻላል ወይ ?

## <u>መደምደሚያ</u>

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ ፩፻፴፰ ዓላማ ሁል ጊዜ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም የሚል ግምት ያለ ለመሆኑ ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ በቁ. ፩፻፲፩ በተደነገገው ልዩ ሥነ ሥርዓት ተጠቁሟል ። ዓላማው የስርቆትንና የከባድ ስርቆትን ወንጀሎች በሚመለከት ረገድ ምን ጊዜም ተግባራዊ እንደማይሆን በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት በቁ ፩፻፲ አስቀድሞ ታይ ቷል ።

ነገር ግን ከላይ እንዳየነው ሁሉ ፣ የተለየ ሥነ ሥርዓቱ ዓላማ ቁ. ፩፻፴፰ትን በተግባር በመተርጎም የአንድ ተከሳሽ የበፊት ጥፋቶች በተከሰሰበት ክስ በማስረጃ ጥፋተኛ ሆኖ ከመገኘቱ በፊት ፍርድ ቤቱን ጥፋት ፈጽሟል ወደሚል አጉል ግምት እንዳያመሩት ለማድረግ ነው ። ዳኛ ሰው ነውና የዚህ ዓይነቱ ግምት በጥፋተኛነት ውሳኔ አሰጣጡ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድ ርበት እንደሚችል አያጠራጥርም ። ስለዚህ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ. ፩፻፴፰ ዓላማ ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች ምክንያት በሚ ከብድ በማንኛውም ወንጀል ሁሉ ተፈጻሚነት ቢኖ ረው ትክክለኛ ፍትሕን ለማስገኘት የሚያስችል መሣ ሪያ ስለሆነ የሕግና ፍትሕ ሚኒስቴር ፣ የሕግ ማሻሻያ ኮሚቴ በጉዳዩ ቢያስብበት ጠቃሚ እንደሚሆን ጸሐ ፊው ያምናል ።

---

12 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት አንደኛ ሠንጠረዥ ማሻሻያ ደንብ ፣ ፲፱፻፹፮ ዓ/ም ቁ ፫ ፣ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁ ፲፮ <u>ነጋሪት ጋዜጣ</u> ፣ ፴፱ኛ ዓመት ፣ ቁ ፴፰ ።